# ማስተካከያ እርማት

## ከጌታቸው ረዳ

ይድረስ ለሠዓሊ አምሳሉ ገብረኪዳን በሚል በጻፍኩት ላይ የገደፍኳቸው ማጣቀሻዎች ስለነበሩ አስቀድሜ ከጠቀስኳቸው ማጣቀሻ እንዲጨመር ለአንባቢዎቼ አሳስባለሁ።

እነኚያ የረሳሁዋቸው ሁለት ቁም ነገሮችም እነሆ።

<< ምድረ አይባ ላይ ሰፈሩ። ጉልሳ ከምትባል ተራራ ስር የባህ መቅደስን (= ቤተ ክርስቲያንን) ሠሩ። ከዚያ አልፈው ምድረ ሐረማት ደረሱ። እዚያ ሐውዜን የምትባል መቅደስ (= ቤተ ክርስቲያን) ሠሩ። እዚያ ባሉበት ጊዜ የትግሬ ሰዎች እዚያ እያሉ አብርሃና አጽብሐ የአክሱም ካህናትን እንዲህ አሏቸው፤ "ከሄድን ጀምሮ ጠላት መጥቷልን?" ከህናቱ፤ "አዎን፤ ይመጣሉ ይሄዳሉ፤ በሆነው ሁሉ ያስቸግሩናል።" ከዚያ ወደ አክሱም ቦታ ሄዱ። እዚያም ሰይጣን እንዳይቀርብ በመስቀል አምሳያ ሐውልት አቆሙ። ከዚያ አልፈው በጽራዕ ምድር ሰፈሩና ከባሕሩ ዳር ውቅሮ የምትባል መቅደስ (= ቤተ ክርስቲያን) ሠሩ። ደግሞ መልኳ ያማረ ቀድመው ከተሠሩና ከተሰወሩ ከመቅደሶች (= ቤተ ክርስቲያኖች) ሁሉ የሚማሰላት የሌለ አንድ መቅደስ (= ቤተ ክርስቲያን) በመደቄ ሠሩ። በአጽሊ ምድር።>>

"ገድል ወስምዕ ዘአብርሃ ወአጽብሐ ነገሥተ አክሱም ዘነበቦ በመንፈስ ቅዱስ አባ ሰላማ ጳጳስ ዘኢትዮጵያ" [Contending and Maryrdom of A and A, Kings of Aksum, which Abba Selama, Bishop of Ethiopia uttered by the Holy Spirit] የሚባል መጽሐፍ አለ።

2- አማራና ትግሬ ከአንድ የነገድ ሥር ስለመገኘታቸው ምክንያት በጣምራ የመጀመሪያው የሕዝብ ቈጠራ የተደረገው በንጉሡ ዘመን ነው። ወጪውን የቻለው ሥራውን ያካሄደው የተባበሩት መንግሥታት ነው። ከዚያ በፊት ከዚያ ወዲህ ያን የመሰለ ቈጠራ አልተካሄደም። በየዓሥር ዓመቱ የሚወጣው ያንን መሠረት አድርጎ ነው የሚል ሊቃውንቶቻችን ይናገራሉ።
አመሰግናለሁ
ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሠማይ ድረገጽ አዘጋጅ) getachre@aol.com